የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፶፱
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 59
ADDIS ABABA 27th August, 2012

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፱/፪ሺ፬ ዓ.ም

የማስታወቂያ አዋጅ …… ገጽ ፮ሺ፭፻፳

CONTENTS

Proclamation No.759/2012

Advertisement Proclamation. …….Page 6520

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፱/፪ሺ፬

## ስለማስታወቂያ የወጣ አዋጅ

ማስታወቂያ ሕብረተሰቡ በምርት ግብይት ወይም በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽእኖ በማሳደር ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ፤

አገሪቱ በገበያ መር የኢኮኖሚ ሥርዓት የምትመራ ከመሆኑ አንጻር ገበያው ጤናማ በሆነ ውድድር እንዲመራ በማድረግ ረገድ ማስታወቂያ ከፍተኛ አስተዋፆ የሚያደርግ በመሆኑ፤

ማስታወቂያ በሥርዓት ካልተመራ የሕብረተሰቡን መብትና ጥቅም እንዲሁም የአገርን ገጽታ ሊጎዳ የሚችል በመሆኑ፤

የማስታወቂያ ወኪሎች፣ የማስታወቂያ አሰራጮች እና የማስታወቂያ አስነጋሪዎችን መብት እና ግዴታን በግልጽ መወሰን በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፱/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 759/2012

## A PROCLAMATION ON ADVERTISEMENT

WHEREAS, advertisement plays a significant role in the economic, social and political development of the country, by influencing the activities of the public in commodity exchange or service rendering;

WHEREAS, advertisement makes a significant contribution in establishing healthy market competition in the market-led economic system of the country;

WHEREAS, advertisement, if not regulated, may harm the rights and interest of the people and the image of the country;

WHEREAS, it is necessary to clearly define the rights and obligations of advertising agents, advertisement disseminators and advertisers;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Advertisement Proclamation No.759/2012".

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ “ማስታወቂያ” ማለት የምርት ወይም የአገልግሎት ሽያጭ እንዲስፋፋ ወይም ስም፣ አርማ፣ የንግድ ምልክት ወይም አላማ እንዲተዋወቅ በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ የንግድ ማስታወቂያ ሲሆን የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያንና የግል ማስታወቂያን ይጨምራል፤

፪/ “የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ” ማለት መገናኛ ብዙሃንን፣ የውጭ ማስታወቂያን፣ የቴሌኮምን፣ የፖስታ፣ የኢንተርኔት ድረ ገፅ እና የፋክስ አገልግሎቶችን፣ ሲኒማን፣ ፊልምን፣ ቪዲዮን እና መሰል የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድን ይጨምራል፤

፫/ “የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ” ማለት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል በመገናኛ ብዙሃን የሚሠራጭ መልዕክት ነው፤

፬/ “የግል ማስታወቂያ” ማለት በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ የአፋልጉኝ ማስታወቂያ፣ የሃዘን መግለጫ እና ሌላ መሰል ማስታወቂያን ያካትታል፤

፭/ “የማስታወቂያ ሥራ” ማለት ማስታወቂያ ማዘጋጀትንና ማሰራጨትን፣ የፕሮሞሽን አገልግሎትን እና ከማስታወቂያ ጋር ተያያዥነት ያለውን ሌላ ሥራ የሚያካትት ሥራ ነው፤

፮/ “የማስታወቂያ ወኪል” ማለት በማስታወቂያ ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው፤

፯/ “የማስታወቂያ አሰራጭ” ማለት በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የአየር ጊዜ፣ የሕትመት ሽፋን ወይም መሰል አገልግሎት በመስጠት ማስታወቂያ የሚያሰራጭ ሰው ነው፤

፰/ “የማስታወቂያ አስነጋሪ” ማለት በማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት ማስታወቂያ የሚተዋወቅለት ሰው ነው፤

፱/ “መገናኛ ብዙሃን” ማለት የሕትመት መገናኛ ብዙሃን እና የብሮድካስት አገልግሎትን ያካትታል፤

## 2. Definition

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ “advertisement” means a commercial advertisement which is disseminated through the means of advertisement dissemination to promote sales of goods or services or to publicize name, logo, trademark or objectives, and includes public and private advertisements;

2/ “means of advertisement dissemination” includes the mass media, outdoor advertisement, telecom, postal, internet web site and fax services, cinema, film, video and any other related means of advertisement dissemination;

3/ “public advertisement” means message in the public interest disseminated by the mass media;

4/ “personal advertisement” means an advertisement advertised through the means of advertisement dissemination and it includes looking for missing person advertisement, condolence message, and other similar advertisement;

5/ “advertising activity” means an activity that includes production and dissemination of advertisements, promotional services and other related activities;

6/ “advertising agent” means a person who undertakes advertising activity;

7/ “advertisement disseminator” means a person who disseminates advertisements through the use of means of advertisement dissemination by providing air time, column coverage or other related services;

8/ “advertiser” means a person whose advertisement is advertised through the means of advertisement dissemination;

9/ “mass media” includes print media and broadcasting services;

፲/ "የሕትመት መገናኛ ብዙሃን" ማለት በጠቅላላው ኅብረተሰብ ወይም በአንድ በተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል እንዲነበብ ታስቦ የሚሰራጭ ማንኛውም ሕትመት ሲሆን ጋዜጣን፣ መጽሔትን፣ የማስታወቂያ መፅሀፍ ወይም የሎው ፔጅን፣ የስልክ ቁጥር ማውጫ ወይም ግሪን ፔጅን ያካትታል፤

፲፩/ "የብሮድካስት አገልግሎት" ማለት የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ሥርጭት አገልግሎት ነው፤

፲፪/ "የውጭ ማስታወቂያ" ማለት፡-

ሀ) በቢልቦርድ፣ በኤሌክትሮኒክ ስክሪን ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል የሚሰራጭ፤

ለ) በሕንጻ ወይም በማናቸውም ስትራክቸር ወይም በትራንስፖርት ተሽከርካሪ ላይ የሚፃፍ ወይም የሚለጠፍ፤

ሐ) በተንጠልጣይ ነገር፣ በፖስተር፣ በስቲከር፣ በብሮሸር፣ ሊፍሌት ወይም በራሪ ወረቀት የሚሰራጭ፤

መ) በድምጽ ካሴት፣ በድምፅ ማጉያ መሳሪያ የሚሰራጭ፤ ወይም

ሠ) በሌላ መሰል ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ፤

ማስታወቂያ ነው፡፡

፲፫/ "በስፖንሰር የሚቀርብ ፕሮግራም" ማለት ፕሮግራሙን ለማሰራጨት ገንዘብ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተከፈለበት ወይም የክፍያ ቃል የተገባበት ፕሮግራም ነው፤

፲፬/ "ስፖንሰር" ማለት ፕሮግራምን ወይም የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድን ስፖንሰር የሚያደርግ ሰው ነው፤

፲፭/ "በፕሮግራም መልክ የሚሠራጭ ማስታወቂያ" ማለት ከሁለት ደቂቃ የበለጠ ጊዜ የሚወስድና ለብሮድካስተሩ ክፍያ የፈፀመ ሰውን ምርት፣ አገልግሎት ወይም መሰል መልእክት በፕሮግራም መልክ ተዘጋጅቶ በብሮድካስት አገልግሎት የሚሰራጭ ማስታወቂያ ነው፤

፲፮/ "ተካታች ማስታወቂያ" ማለት ብሮድካስተሩ ገንዘብ የተቀበለበትን ወይም ጥቅም ያገኘበትን የማንኛውንም ሰው ምርት፣ አገልግሎት ወይም መሰል መልእክት በተዘዋዋሪ ለማስተዋወቅ በፅሁፍ፣ በድምጽ ወይም በምስል ከአንድ ፕሮግራም ጋር የተካተተ ማስታወቂያ ነው፤

10/ "print media" means any printed material which has a distribution aimed to reach the entire public or a section thereof such as a newspaper, magazine, advertisement book or yellow page, telephone directory or green page;

11/ "broadcasting service" means a radio or television transmission service;

12/ "outdoor advertisement" means any advertisement:

a) disseminated by using billboard, electronic screen or moving picture;

b) written or affixed to a building or any structure or transport vehicle;

c) disseminated by using banner, poster, sticker, brochure, leaflets or flier;

d) disseminated through audio cassette, loud speaker; or

e) disseminated through any other related means of dissemination.

13/ "sponsored program" means a program the transmission cost of which is either directly or indirectly paid or promised;

14/ "sponsor" means a person who sponsors a program or a means of advertisement dissemination;

15/ "infomercial" means an advertisement consuming more than two minutes, that is disseminated through a broadcasting service after being prepared in a program format so as to promote the product, service or similar message of the contracting party who agreed to pay to the broadcaster for such service;

16/ "inserted advertisement" means an advertisement inserted with a program in the form of script, sound or image to promote indirectly the product, service or similar message of any person, from whom the broadcaster has earned money or obtained benefit;

፲፯/ “ተጓዳኝ ማስታወቂያ” ማለት በቴሌቪዥን መስኮት ወይም ስክሪን ከሚሰራጨው ፕሮግራም ጋር አልፎ አልፎ በተጓዳኝ መስኮት የሚታይ ማስታወቂያ ነው፤

፲፰/ “የአፀፋ ማስታወቂያ” ማለት የዚህን አዋጅ ድንጋጌ በሚጥስ ማስታወቂያ የተነሳ በህዝብ ዘንድ የተፈጠረውን የተሳሳተ አመለካከት ለማቃናት ወይም ለጉዳት የተጋለጠውን ወገን መብት ለማስጠበቅ የሚሰራጭ ማስታወቂያ ነው፤

፲፱/ “ፕሮግራም” ማለት በድምፅ ወይም በምስል ወይም በሁለቱ ተቀነባብሮ ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት ወይም ሁሉንም አካቶ በብሮድካስት አገልግሎት የሚቀርብ ስርጭት ነው፤

፳/ “የዜና እና የወቅታዊ ጉዳዮች ዘገባ” ማለት አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ አገራዊ ወይም አለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው እና ወቅታዊ የሆኑ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማኅበራዊ ጉዳዮችን በሚመለከት በብሮድካስት አገልግሎት የሚቀርብ ዜና፣ ዘገባ፣ ማብራሪያ፣ ትርጓሜ፣ አስተያየት፣ ሐተታ ወይም ትንታኔ ነው፤

፳፩/ “እለታዊ የስርጭት ጊዜ” ማለት ከንጋቱ ፲፪ ሰዓት ጀምሮ ባሉት ፳፬ ሰዓታት የሚተላለፍ የብሮድካስት አገልግሎት ስርጭት ነው፤

፳፪/ “ሎተሪ” ማለት የሽልማት አሸናፊው በእድል፣ በእጣ አወጣጥ ወይም በማናቸውም ሌላ ዘዴ የሚታወቅበት ጨዋታ ወይም ድርጊት ሲሆን አግባብ ባለው ሕግ የተመለከቱትን ጨዋታዎችና ድርጊቶች ያካትታል፤

፳፫/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፳፬/ “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ነው፤

፳፭/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፮/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

17/ “split-screen advertisement” means an advertisement displayed occasionally on the same screen adjacent to a program disseminated through television window or screen;

18/ “counter advertisement” means an advertisement disseminated to counter wrong public opinion created by previously transmitted advertisement in breach of the provision of this Proclamation or to protect the rights of the victim of such violation;

19/ “program” means voice or visual or audiovisual arrangement transmitted to inform, educate or entertain the public or an all inclusive transmission of a broadcasting service;

20/ “news and current affairs program” means news, documentary, commentary, interpretation, feature or analysis transmitted through broadcasting service that has local, regional, national or international content and that relates to immediate political, economical or social issues;

21/ “daily transmission time” means broadcasting service transmission in 24 hours starting from 6 a.m.;

22/ “lottery” means any game or activity in which the prize winner is determined by chance, drawing of lots or any other means, and includes games and events listed by the relevant law;

23/ “region” means any of the states referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

24/ “Authority” means the Ethiopian Broadcasting Authority;

25/ “person” means a physical or juridical person;

26/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

፫. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡-

፩/ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሠራ የማስታወቂያ ወኪል፣ የማስታወቂያ አሰራጭ እና የማስታወቂያ አስነጋሪ፤

፪/ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚዘጋጅና በሚሰራጭ ማስታወቂያ፤

፫/ በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ ድርጅት ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ በሚኖር ሰው አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በውጭ አገር በተቋቋመ የኢንተርኔት ድረ ገፅ ላይ በሚሰራጭ ማስታወቂያ፤

፬/ አገር ውስጥ ለማሰራጨት ሲባል ወደ ኢትዮጵያ በሚገባ እና ዋነኛ አትኩሮቱ በአገር ውስጥ ጉዳዮች ላይ በሆነ ማናቸውም የውጭ አገር ጋዜጣ ወይም መፅሄት አማካኝነት በሚሰራጭ ማስታወቂያ፤ እና

፭/ በአገር ውስጥ ተዘጋጅቶ በውጭ አገር የብሮድካስት አገልግሎት ወደ አገር ውስጥ በሚሰራጭ ማስታወቂያ።

## ክፍል ሁለት

## በማስታወቂያ ሥራ ስለመሰማራት

፬. **በማስታወቂያ ሥራ የመሰማራት መብት**

፩/ ማንኛውም ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ግለሰብ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተቋቋመና በካፒታሉ ውስጥ የውጭ አገር ዜጋ ድርሻ የሌለበት የንግድ ማኅበር በማስታወቂያ ሥራ የመሰማራት መብት ይኖረዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ በማስታወቂያ ሥራ የመሰማራት መብት ይኖረዋል፡፡

፭. **የማስታወቂያ ሥራ ፈቃድ ስለማውጣት**

፩/ በማስታወቂያ ወኪልነት ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው የመንግስት አካል የማስታወቂያ ሥራ ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም ማስታወቂያ አሠራጭ ማስታወቂያ በማዘጋጀት ሥራ ላይ ለመሰማራት አግባብ ካለው የመንግስት አካል የማስታወቂያ ሥራ ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

3. **Scope of Application**

This Proclamation shall be applicable to:

1/ advertising agent, advertisement disseminator and advertiser working within Ethiopia;

2/ advertisement prepared and disseminated in Ethiopia;

3/ advertisement disseminated through the internet website being designed in Ethiopia or abroad, by an organization established in Ethiopia or by a person who resides in Ethiopia;

4/ advertisement disseminated through any foreign news paper or magazine imported and which focuses primarily on domestic issues; and

5/ advertisement produced in Ethiopia primarily for local audience and disseminated from abroad by a foreign broadcasting entity.

## PART TWO

## UNDERTAKING ADVERTISING ACTIVITY

4. **The Right to Undertake Advertisement Activity**

1/ Any Ethiopian national or a business organization established in accordance with the Ethiopian law and whose capital is not shared by foreign nationals, shall have the right to undertake advertising activity.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, any foreign national of Ethiopian origin shall have the right to engage in advertising activity.

5. **Obtaining Advertising Business License**

1/ Any person who wants to engage in the activities of an advertising agent shall have to obtain an advertising business license from the appropriate governmental body.

2/ Any advertisement disseminator who wants to engage in the production of advertisement shall have to obtain advertising business license from the appropriate governmental body.

፫/ ማስታወቂያ በማዘጋጀት ሥራ ላይ የሚሰማራ ማንኛውም የመገናኛ ብዙሃን የማስታወቂያ ሥራውን ከመገናኛ ብዙሃን ሥራው በተለየ አደረጃጀት ማከናወን አለበት።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም ምርቱ፣ አገልግሎቱ ወይም ሌላ መልዕክት እንዲተዋወቅለት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የማስታወቂያ ሥራ ፈቃድ ማውጣት ሳያስፈልገው የራሱን ማስታወቂያ አዘጋጅቶ ማሰራጨት ወይም ማስታወቂያውን አዘጋጅቶ በማስታወቂያ አሰራጭ አማካኝነት እንዲሰራጭለት ማድረግ ይችላል፡፡ በማስታወቂያው ላይም ማንነቱን እና አድራሻውን በግልፅ ማካተት አለበት፡፡

፭/ ማንኛውም በውጭ አገር ተዘጋጅቶ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ማስታወቂያ እንዲሰራጭ ሊደረግ የሚችለው በማስታወቂያ ወኪል አማካኝነት ነው፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሰረት ፈቃድ የሚሰጥ አግባብ ያለው የመንግስት አካል ባለፈቃዶቹን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለዚሁ ጉዳይ የተዘጋጀን ቅፅ በመሙላት ለባለሥልጣኑ ማስተላለፍ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለማስታወቂያ በጠቅላላው

### ፮. ስለማስታወቂያ ይዘትና አቀራረብ

፩/ ማንኛውም ማስታወቂያ፡-

ሀ) ማንኛውንም ሕግ ወይም መልካም ሥነ ምግባር የማይጻረር፤

ለ) አሳሳች ወይም ተገቢ ካልሆነ አገላለጽ ነፃ የሆነ፤

ሐ) የሕብረተሰቡን ማህበራዊና ባህላዊ እሴት የሚያከብርና የሸማቹን ሕጋዊ ጥቅም የማይጎዳ፤

መ) የሚተዋወቀውን ምርት ወይም አገልግሎት እውነተኛ ባህሪ፣ ጥቅም፣ ጥራትና ሌላ መሰል መረጃዎችን የሚገልጽ፤

ሠ) የሌሎችን ሰዎች ምርት ወይም አገልግሎት የማያንቋሽሽ፤

3/ Any mass media that engages in the production of advertisement shall conduct the advertising activity in a separate arrangement from its mass media activity.

4/ Notwithstanding sub-article (1) and (2) of this Article, any person who wants to promote his product, service or other message, may prepare and disseminate his own advertisement or prepare and disseminate it through an advertisement disseminator, without required to have advertising business license. Provided, however, that he shall include his identity and address in the advertisement.

5/ Any advertisement prepared abroad may be disseminated in Ethiopia through an advertising agent.

6/ The appropriate governmental body that issue license pursuant to sub-article (1) and (2) of this Article shall transmit to the Authority information concerning the license holders by filling a form designed for such purpose.

## PART THREE

## ADVERTISEMENT IN GENERAL

### 6. Content and Presentation of Advertisement

1/ Any advertisement shall, in its content and presentation:

a) not be contrary to the law or moral;

b) be free from misleading or unfair statements;

c) respect the social and traditional values of the society and not infringe the legitimate interests of consumers;

d) describe the true nature, use, quality and other similar information of the product or service intended to be promoted;

e) not undermine the commodities or services of other persons;

ረ) የአገርን ክብርና ጥቅም የሚጠብቅ፣ እና

ሰ) የሙያ ሥነ ምግባርን የሚያከብር፣

ይዘትና አቀራረብ ያለው መሆን አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የሚሰራጭ ማስታወቂያ ከሌሎች ፕሮግራሞች የተለየ መሆኑ በግልጽ እንዲታወቅ ሆኖ መቅረብ ያለበት ሲሆን በፕሮግራሞቹ ይዘት ላይም ተፅእኖ ማድረግ የለበትም፡፡

፫/ ማስታወቂያ በዜና መልክ መዘጋጀትና መሰራጨት የለበትም።

፬/ የማስታወቂያ ወኪል የአንድን ሰው ምርት፣ አገልግሎት ወይም ሌላ መልእክት የሚያስተ ዋውቅ የንግድ ማስታወቂያ አዘጋጅቶ ባሰራጨ በሦስት ወራት ውስጥ የሌላ ሰውን ተመሳሳይ ምርት፣ አገልግሎት ወይም ሌላ መልእክት በተመሳሳይ የማስታወቂያ ተዋናይ ምስል ወይም ድምፅ አዘጋጅቶ ማሰራጨት የለበትም።

፭/ ለቅጅና ተዛማጅ መብቶች እንዲሁም ለፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና የኢንዱስትሪያዊ ንድፍ ውጤቶች መብት ጥበቃ የወጡ ሕግጋት በማስታወቂያ ሥራ ላይ እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ፯. ሕግን ወይም መልካም ሥነ ምግባርን ስለሚፃረር ማስታወቂያ

የሚከተሉት ማስታወቂያዎች ሕግን ወይም መልካም ሥነ ምግባርን የሚጻረር ይዘት ወይም አቀራረብ እንዳላቸው ሆነው ይቆጠራሉ፡-

፩/ ቋንቋን፣ ፆታን፣ ዘርን፣ ብሔርን፣ ብሔረሰብን፣ ሙያን፣ ሐይማኖትን፣ እምነትን፣ ፖለቲካዊ ወይም ማኅበራዊ አቋምን አስመልክቶ የሰው ልጅን ስብዕና፣ ነጻነት ወይም እኩልነት የሚጻረር ምስልን፣ አነጋገርን ወይም ንጽጽርን የያዘ ማስታወቂያ፣

፪/ የግለሰብን፣ የብሔርን፣ የብሔረሰብን ወይም የሕዝብን መልካም ሥነ ምግባር ወይም ሰብዓዊ ክብርን እንዲሁም የድርጅትን መልካም ስምና ዝና የሚያጎድፍ ማስታወቂያ፣

፫/ ብሔራዊ ወይም የክልል ሰንደቅ ዓላማን፣ አርማን፣ ብሔራዊ መዝሙርን ወይም ገንዘብን የሚያንቋሽሽ ወይም የሚያዋርድ ማስታወቂያ፣

f) protect the dignity and interests of the country; and

g) respect professional code of conduct.

2/ Any advertisement disseminated through the mass media shall be presented in a manner that clearly differentiates it from other programs and may not affect the content of the programs.

3/ Advertisement may not be prepared and disseminated in the form of news.

4/ An advertising agent who designed and disseminated an advertisement to promote the goods, services or other related messages of any person may not advertise, within the next three months, similar goods, services or other related messages of another person by using the image or voice of the same advertising actor.

5/ Laws issued to protect copyright and neighboring rights as well as inventions, minor inventions and industrial design patent shall be applicable with respect to advertisement service as appropriate.

## 7. Unlawful or Immoral Advertisement

The following advertisements shall be deemed to be as having unlawful or immoral content or presentation:

1/ advertisement that contains image, speech or comparisons that violates the dignity, liberty or equality of mankind in relation to language, gender, race, nation, nationality, profession, religion, belief, political or social status;

2/ advertisement that violates the rules of good behavior or human dignity of individuals, nation, nationalities or peoples, and defames the reputation of an organization;

3/ advertisement that undermine the national or regional state’s flag, emblem, national anthem or currency;

፬/ የአካል ጉዳተኛን፣ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደሙ ውስጥ ያለበትን ወይም በሌላ ህመም የተያዘ ሰውን ክብርና ሥነ ልቦና የሚነካ ማስታወቂያ፤

፭/ በሕብረተሰቡ መካከል አመጽ፣ የሀይል ተግባር፣ ሽብር፣ ግጭት ወይም የፍርሀት ስሜት እንዲፈጠር የሚያነሳሳ ማስታወቂያ፤

፮/ የሕብረተሰቡን አካላዊና አእምሯዊ ጤንነት ወይም ደህንነት ለጉዳት የሚያጋልጥ ድርጊት እንዲፈጸም የሚያነሳሳ ማስታወቂያ፤

፯/ አግባብ ያለው የመንግስት አካል የሚወስነውን የድምፅ መጠን በመተላለፍ በማናቸውም አይነት የድምፅ ማጉያ መሳሪያ አማካኝነት አካባቢን በከፍተኛ ድምፅ በመበከል የሚሰራጭ ማስታወቂያ፤

፰/ ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆነ የጽሑፍ መልእክት፣ ምስል፣ ስዕላዊ መግለጫ፣ ፊልም ወይም መሰል አቀራረብን የያዘ ማስታወቂያ፤

፱/ የግለሰብን ስም፣ ምስል ወይም ፎቶግራፍ ግለሰቡ ሳይፈቅድ የሚጠቀም ወይም በሕግ ጥበቃ የሚደረግለትን የኪነጥበብ ወይም የፈጠራ ሥራ የሚመለከተው ሰው ሳይፈቅድ የሚጠቀም ማስታወቂያ፤

፲/ ለትራፊክ ደህንነት ወይም ለአካባቢ ጥበቃ ተጻራሪ የሆነ ማስታወቂያ፤

፲፩/ የመከላከያ ሰራዊት ወይም የፖሊስ የደንብ ልብስን፣ ምልክትን ወይም ሽልማትን በመልበስ ወይም በማድረግ የሚቀርብ የንግድ ማስታወቂያ፤

፲፪/ በሌላ ሕግ የተከለከለ ይዘት ወይም አቀራረብ የያዘ ወይም ማንኛውም ሕግ እንዲጣስ የሚያነሳሳ ማስታወቂያ፡፡

## ፰. ስለአሳሳች ወይም ተገቢ ያልሆነ ማስታወቂያ

የሚከተሉት ማስታወቂያዎች አሳሳች ወይም ተገቢ ያልሆነ ይዘት ወይም አቀራረብ እንዳላቸው ሆነው ይቆጠራሉ፡-

፩/ የሚተዋወቀውን ምርት የተመረተበት አገር ወይም ቦታ፣ ቀን፣ የምርቱን ባህሪ፣ በውስጡ የያዘውን ንጥረ ነገር፣ ክብደት፣ መጠን፣ ያለውን ጠቀሜታ ወይም ተቀባይነት በሐሰት የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤



4/ advertisement that undermine the dignity or emotional feeling of physically disabled person or a person living with HIV/AIDS or suffering from other disease;

5/ advertisement that instigates chaos, violence, terror, conflict or fear among people;

6/ advertisement that instigate an action that could endanger the physical or mental health and security of the people;

7/ advertisement causing sound pollution through any sound magnifying machine, which does not comply with the sound limit set by the appropriate governmental body;

8/ advertisement with obscene written message, image, picture, film or similar presentation;

9/ advertisement using the name, image or photograph of a person without his consent, or artistic or creative works protected by the law without authorization by the concerned person;

10/ advertisement contrary to traffic safety or environmental protection;

11/ commercial advertisement presented by wearing defense force or police uniforms, decorations or insignia;

12/ advertisement with content or presentation prohibited by other laws or that promotes the violation of any law.

## 8. Misleading or Unfair Advertisement

The following advertisements shall be deemed to be as having misleading or unfair content or presentation:

1/ advertisement that gives false information about the country or place of origin, date of production, nature, ingredients, weight, volume, use or acceptance by consumers of a product;

፪/ ታክስና ሌላ ሕጋዊ ክፍያን ጨምሮ ምርቱ ወይም አገልግሎቱ የሚሸጥበትን ዋጋ በሚመለከት ወይም ለምርቱ ወይም ለአገልግሎቱ የቅጅ ወይም የፓተንት መብት፣ የጥራትና የደረጃ መሥፈርት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም እውቅና ካለው አካል ሽልማት መገኘቱን ወይም ሌላ መሰል መረጃን በሚመለከት በሐሰት የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤

፫/ አንድ ምርት ወይም አገልግሎት የሌለውን ጥቅም፣ ጥራት፣ መአዛ፣ ጣእም፣ ንጥረ ነገር፣ ጥንካሬ፣ እድሜ ወይም ብርካቴ እንዳለው አስመስሎ የሚያቀርብ ማስታወቂያ፤

፬/ የአገልግሎት ጊዜው ለማለፍ የደረሰን ወይም ያለፈበትን ምርት የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤

፭/ የዱቄት ወተትን ወይም መሰል ምግብን ከስድስት ወር እድሜ በታች ለሆኑ ሕጻናት ከእናት ጡት ወተት የሚመረጥ ወይም የማይተናነስ እንደሆነ አድርጎ የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤

፮/ የሌላ ሰውን ምርት ወይም አገልግሎት እንደራስ አድርጎ የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤

፯/ ተገቢ የሆነ የንግድ ውድድር መርህን በመተላለፍ የሚተዋወቀውን ምርት ወይም አገልግሎት የማይጠቀም ሰውን የሚያንቋሽሽ ማስታወቂያ፤

፰/ አንድን ምርት ወይም አገልግሎት ከሌላ ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በማወዳደር ለንጽጽር የቀረበውን ምርት ወይም አገልግሎት ወይም የተወዳዳሪውን ብቃት ወይም ዝና የሚያንቋሽሽ ወይም የውጭ አገር ምርት ተመራጭ እንዲሆን ለማድረግ ሲባል አገራዊ ምርትን ወይም አገልግሎትን የሚያንቋሽሽ ማስታወቂያ፤

፱/ ከውጭ ቋንቋ የተወሰደው ቃል ማስታወቂያው በተሰራጨበት የአገሪቱ ቋንቋ ፍቺ ከሌለው በቀር የአገሪቱን ቋንቋ ከውጭ አገር ቋንቋ ጋር በማቀላቀል የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤

፲/ በገበያ ውስጥ የሌለ ምርት ወይም አገልግሎት እንዳለ አስመስሎ የሚያቀርብ ማስታወቂያ፤

፲፩/ አንድን ምርት፣ አገልግሎት ወይም ድርጅት ከሌላ ምርት፣ አገልግሎት ወይም ድርጅት ጋር ሊያሳስት የሚችል አሻሚ የሆነ ማስታወቂያ፤

2/ advertisement that gives false information about the price of goods or service including tax and other lawful fees or about obtaining copy right or patent right, quality and standard certification or prize from a recognized body or other related information;

3/ advertisement presenting a product or a service beyond its real usage, quality, flavor, taste, ingredient, strength, durability or sufficiency;

4/ advertisement promoting a product the expiry date of which is approaching or has already lapsed;

5/ advertisement promoting a milk powder or similar meal as preferable or equivalent to breast feeding for children under the age of six months;

6/ advertisement presenting the products or services of others as one's own;

7/ advertisement promoting a product or service contrary to the rules of fair trade competition by undermining those consumers who do not use the product or the service;

8/ advertisement that undermines a product or service, or the capacity or reputation of a competitor by comparing and contrasting it with one's product or service, or that degrades local products or services with the aim of promoting preference to an imported product or service;

9/ advertisement that mix local language with a foreign language unless a term taken from the foreign language has no equivalent in the local language;

10/ advertisement that present goods or services that are not available in the market;

11/ an ambiguous advertisement that confuses a product, service or a company with another product, service or company;

፲፪/ በትክክለኛ ዋጋው እየተሸጠ ያለን ምርት ወይም አገልግሎት በነጻ እየተሰጠ ወይም በቅናሽ እየተሸጠ እንደሆነ አድርጎ የሚያቀርብ ማስታወቂያ፤

፲፫/ ለሽያጭ የቀረቡ አክስዮኖች ያስገኛሉ የሚባለውን እርግጠኛ ያልሆነ የትርፍ ድርሻ የሚያስተዋውቅ ማስታወቂያ፤

፲፬/ ምርት ወይም አገልግሎት ለሚገዛ ደንበኛ ሽልማት ወይም የዋስትና መብት እንደሚሰጥ ተገልጾ ሽልማቱ የማይሰጥበት ወይም ዋስትናው የማይከበርበት ማስታወቂያ፤

፲፭/ የምርምር ውጤትን ወይም ከሳይንሳዊ፣ ከቴክኒካዊ ወይም ከሌላ ሕትመት የተወሰደ መግለጫን ወይም ጥቅስን ከሚተዋወቀው ምርት ወይም አገልግሎት ጋር ግንኙነት ሳይኖረው ግንኙነት እንዳለው አስመስሎ የሚያቀርብ ማስታወቂያ፤

፲፮/ ሐሰተኛ ምስክርነትን የሚጠቀም ማስታወቂያ፤

፲፯/ በማስረጃ ሊረጋገጥ የማይችልን "የመጀመሪያው"፣ "ብቸኛው"፣ "ለመጀመሪያ ጊዜ"፣ "ከዚህ ቀደም ያልነበረ"፣ "ወደር የሌለው" የሚል ወይም መሰል የሆነ ማወዳደሪያን የያዘ ማስታወቂያ፤

፲፰/ መሰል አሳሳች ወይም ተገቢ ያልሆነ ይዘት ወይም አቀራረብ ያለው ማንኛውም ሌላ ማስታወቂያ፡፡

## ፱. የተለየ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለሚያስፈልገው ማስታወቂያ

፩/ አስገዳጅ የደረጃ መስፈርቶችን ማሟላት የሚገባውን ማንኛውንም ምርት ወይም አገልግሎት ለማስተዋወቅ በቅድሚያ አግባብ ካለው አካል የተሰጠ የጥራት ወይም መሰል ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መኖር አለበት፡፡

፪/ የማስታወቂያ አስነጋሪው ለሚያቀርበው ምርት ወይም ለሚሰጠው አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ ማግኘት የሚገባው ከሆነ አግባብ ካለው አካል የምስክር ወረቀቱን ወይም ፈቃዱን ሳያገኝ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ማስተዋወቅ አይችልም፡፡

12/ advertisement announcing the supply of a product or the provision of service freely or at a discounted price while the product is supplied or the service is rendered at its real price;

13/ advertisement promising speculative dividend earnings of shares offered for sale;

14/ advertisement promising the awarding of prizes or the provision of guarantees to consumers and fails to do so after the sale of products or services;

15/ advertisement that presents research results or excerpts or quotations from scientific, technical or other publication as if they have relation with the promoted product or service;

16/ an advertisement which uses false testimony;

17/ advertisement containing superlatives such as "the first of its kind", "the only one", "for the first time", "never ever before", or "unparalleled", if it cannot be proved with evidence;

18/ any other similar advertisement misleading or unfair with its content or presentation.

## 9. Advertisement Requiring Special Certification

1/ Prior certification by the appropriate body shall be required in order to promote products or services that have to meet mandatory standard requirements.

2/ An advertiser who is required to obtain a certificate of competence or a business license may not advertise its product or service without obtaining such certificate or license from the appropriate body.

## ፲. አካለመጠን ያልደረሰ ልጅን ስለሚመለከት ማስታወቂያ

የሚከተሉትን ማስታወቂያዎች ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡-

፩/ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅን አመለካከት፣ ስሜት ወይም አስተሳሰብ ሊጎዳ የሚችል ማስታወቂያ፤

፪/ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ በቤተሰቡ፣ በአሳዳሪው፣ በሞግዚቱ፣ በመምህሩ፣ በሕብረተሰቡ ወይም በአገሩ ላይ ፍቅር ወይም እምነት እንዲያጣ የሚያደርግ ማስታወቂያ፤

፫/ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ በማስታወቂያ የተነገረ ምርትን ወይም አገልግሎትን ቤተሰቡን፣ አሳዳሪውን፣ ሞግዚቱን ወይም ሌላ ሰውን እንዲያስገዛ በግልጽ የሚገፋፋ ማስታወቂያ፤

፬/ በማስታወቂያ የተነገረን ምርት ወይም አገልግሎት ትክክለኛ ያልሆነ ዋጋ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በመግለጽ ምርቱ ወይም አገልግሎቱ በማናቸውም ቤተሰብ ሊገዛ ይችላል የሚል እምነት በአካለመጠን ባልደረሰ ልጅ አእምሮ እንዲቀረጽ የሚያደርግ ማስታወቂያ፤

፭/ በማስታወቂያ የተነገረን ምርት ወይም አገልግሎት የገዛ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ካልገዛ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ የተሻለ እንደሆነ በማስመሰል ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ያልገዛው የዝቅተኝነት ስሜት እንዲሰማው የሚያደርግ ማስታወቂያ፤

፮/ በማስታወቂያ ውስጥ የተለያየ ድምፅን፣ ፅሁፍንና ምስልን በማቀላቀል አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ሕገ ወጥ ወይም ለመልካም ሥነ ምግባር ተፃራሪ የሆነ ተግባር እያከናወነ ወይም በአደገኛ ሁኔታ ወይም ቦታ ውስጥ ሆኖ የሚያሳይ ማስታወቂያ፤

፯/ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅን ያለ አሳዳሪውና ሞግዚቱ ፈቃድ የማስታወቂያ አቅራቢ ወይም ተዋናይ አድርጎ የሚጠቀም ማስታወቂያ፤ ወይም

፰/ መሰል ይዘት ወይም አቀራረብ ያለው ማናቸውንም ሌላ ማስታወቂያ፡፡

## 10. Advertisements Affecting Minors

The dissemination of the following advertisements shall be prohibited:

1/ an advertisement that may harm the attitude, feeling or thinking of a minor;

2/ an advertisement that may cause a minor to lose affection or trust in his family, guardian, tutor, teacher, society or country;

3/ an advertisement that openly motivates a minor to require his parent, guardian, tutor or any other person to buy the advertised product or service;

4/ an advertisement which directly or indirectly provides a misleading price and gives impression to a minor that the product or service advertised is affordable to any family;

5/ an advertisement causing inferiority complex to a minor that did not buy the advertised product or service, by portraying that the one who does is better than the one who does not;

6/ an advertisement that demonstrates, through mixing of sounds, writings and pictures, a minor while doing any action contrary to law or moral, or being in a dangerous situation or place;

7/ an advertisement that uses a minor as an advertisement presenter or actor without the consent of his guardian or tutor; or

8/ any other advertisement having similar content or presentation.

## ፲፩. ስለፀረ አረም ወይም ፀረ ተባይ ማስታወቂያ

የፀረ አረም ወይም የፀረ ተባይ ማስታወቂያ፡-

፩/ አጠቃቀሙን የተመለከተና በአጠቃቀሙ ጊዜ መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ የሚገልፅ ግልጽና ትክክለኛ መረጃ መስጠት አለበት፤

፪/ ሙሉ በሙሉ መርዛማ እንዳልሆነ እና ለጤና ጎጂ እንዳልሆነ ተደርጎ መሠራጨት የለበትም።

## ፲፪. ሎተሪን ስለሚመለከት ማስታወቂያ

፩/ ማንኛውም ሰው ሎተሪን የሚመለከት ማስታወቂያ ለማስተዋወቅ የሚችለው በሕግ ወይም አግባብ ባለው የመንግስት አካል የሎተሪን ሥራ ለማካሄድ የተሰጠ ፈቃድ ሲኖረው ነው፡፡

፪/ ማንኛውም የሎተሪ ማስታወቂያ፡-

ሀ) እጣውን ያዘጋጀው ሰው ስምና ሕጋዊ ፈቃድ ያለው መሆኑን፤

ለ) እጣው የሚያስገኘውን የገንዘብ መጠን ወይም የሽልማት አይነት፤ እና

ሐ) እጣው የሚወጣበትን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ፤

መግለጽ አለበት፡፡

## ፲፫. ስለሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ

፩/ የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ የማንኛውንም ሰው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ፣ ምርት፣ አገልግሎት ወይም መሰል መልእክት የሚያስተዋውቅ መሆን የለበትም፡፡

፪/ በማስታወቂያ አሰራጭ ለሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ የሚጠየቀው ክፍያ ለንግድ ማስታወቂያ ከሚጠየቀው ክፍያ መብለጥ የለበትም፡፡

፫/ ማንኛውም የማስታወቂያ አሠራጭ የሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያን ከንግድ ማስታወቂያ ቅድሚያ በመስጠት በማስታወቂያ አስነጋሪው ምርጫ መሰረት ማሠራጨት አለበት፡፡

፬/ የማስታወቂያ አሰራጩ ለሕዝብ አገልግሎት ማስታወቂያ ቅድሚያ በመስጠቱ ከማስታወቂያ ወኪል ወይም ከማስታወቂያ አስነጋሪ ጋር በገባው ውል መሰረት መሰራጨት የነበረበት ሌላ ማስታወቂያ ሳይሰራጭ ቢቀር ይህንኑ ለማስታወቂያ ወኪሉ ወይም ለማስታወቂያ አስነጋሪው አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 11. Herbicides or Pesticides Advertisement

Herbicides or pesticides advertisement:

1/ shall provide clear and accurate information about their usage and the precautions to be taken during their usage;

2/ may not be disseminated as the product is not totally poisonous and not harmful to health.

## 12. Lottery Advertisement

1/ Any person who is not authorized by the law or a permission obtained from the appropriate government body to engage in a lottery business may not advertise a lottery.

2/ Any lottery advertisement shall disclose:

a) the name of the lot organizing person and that it has a legal permission;

b) the amount of money or prize type to be awarded; and

c) the date, time, and venue of lot casting.

## 13. Public Advertisement

1/ A public advertisement may not advertise a business activity, product, service or related message of any person.

2/ The amount of money to be charged by an advertisement disseminator for public advertisement may not exceed that of commercial advertisement.

3/ Any advertisement disseminator shall give priority to public advertisement than commercial advertisement, and disseminate it based on the choice of the advertiser.

4/ If an advertisement disseminator fails, due to the priority given to a public advertisement, to disseminate another advertisement in accordance with a contract concluded with an advertising agent or an advertiser, it shall, in advance, inform the advertising agent or the advertiser.

**፲፬. የአፀፋ ማስታወቂያ**

፩/ የማስታወቂያ አስነጋሪው፣ የማስታወቂያ ወኪሉ እና የማስታወቂያ አሰራጩ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በሚጥስ ማስታወቂያ የተነሳ መብቱ የተነካበትንና ለጉዳት የተጋለጠውን ወገን ሕጋዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የአፀፋ ማስታወቂያ ማውጣት አለባቸው፡፡

፪/ የማስታወቂያ አስነጋሪው፣ የማስታወቂያ ወኪሉ እና የማስታወቂያ አሰራጩ ተቃራኒ ማስረጃ እስካላቀረቡ ድረስ የአፀፋ ማስታወቂያውን ለማውጣት የሚያስፈልገውን ወጪ በማይከፋፈል ኃላፊነት ይሸፍናሉ፡፡

፫/ የአፀፋው ማስታወቂያ ቀደምሲል የተሰራጨው ማስታወቂያ በተዘጋጀበትና በተሰራጨበት መንገድ፣ በቆየበት ጊዜ እና በተሰራጨበት አካባቢ በተመሳሳይ ሁኔታ መሠራጨት አለበት፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው ሌላ አካል አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው የአፀፋ ማስታወቂያው የተሰራጨበት ዘዴ፣ የቆየበት ጊዜ እና የተሰራጨበት አካባቢን በተመለከተ ለውጥ እንዲደረግ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## **ክፍል አራት**

## **ስፖንሰርሺፕ**

**፲፭. በስፖንሰር ስለሚቀርብ ፕሮግራም**

፩/ በስፖንሰር የሚቀርብ ፕሮግራም ይዘት ወይም የጊዜ ሰሌዳ በስፖንሰሩ ተፅእኖ ስር መውደቅ የለበትም፡፡ በተለይም በፕሮግራሙ ይዘት ውስጥ የስፖንሰሩ ምርት ወይም አገልግሎት እንዲሸጥ ወይም እንዲከራይ መቀስቀስ የለበትም፡፡

፪/ በስፖንሰር በሚቀርብ ፕሮግራም የስፖንሰር አድራጊው ስም፣ አላማ፣ አገልግሎት፣ ምርት እና መሠል ሁኔታዎች ወይም ለስፖንሰሩ የሚቀርብ ምስጋና በፕሮግራሙ መጀመሪያ፣ አካፋይ ወይም መጨረሻ ላይ ሊተዋወቅ ወይም ሊገለፅ ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፯(፩) እና አንቀፅ ፲፱ የተደነገገው ቢኖርም ተጓዳኝ፣ በፕሮግራም መልክ የሚሰራጭ ማስታወቂያን፣ የስፖንሰር አድራጊውን ስም፣ አላማ፣ አገልግሎት፣ የምርት እና መሰል መልእክቶችን እንዲሁም የምስጋና መግለጫን ጨምሮ ለማንኛውም ማስታወቂያ የሚመደበው ጊዜ ስፖንሰር ከተደረገው ፕሮግራም የስርጭት ጊዜ ውስጥ ከ፲ በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

**14. Counter Advertisement**

1/ The advertiser, the advertising agent and the advertisement disseminator shall disseminate a counter advertisement in favour of the victim of any advertisement that breaches any of the provisions of this Proclamation.

2/ Unless otherwise contrary evidence is presented, the advertiser, the advertising agent and the advertisement disseminator shall be jointly and severally liable to cover the cost of the counter advertisement.

3/ A counter advertisement shall be arranged and disseminated in the same method, duration and place as the original advertisement was disseminated.

4/ If it is found necessary, the Authority or other appropriate body may order a change on the method, duration and place of dissemination of the counter advertisement.

## **PART FOUR**

## **SPONSORSHIP**

**15. Sponsored Program**

1/ The content or timetable of a sponsored program may not fall under the influence of the sponsor. In particular, a sponsored program may not agitate the sell or hire of the sponsor’s product or service.

2/ A sponsored program may advertise or announce the name, objectives, service, goods and similar condition or acknowledgement of the sponsor at the beginning, break time or end of the program; however, notwithstanding to the provisions of Article 17(1) and Article 19 of this Proclamation, the time to be allocated for any advertisement including split-screen, and infomercial advertisement, the name, objective, service, goods and similar messages as well as, acknowledgement of a sponsor may not exceed 10 percent of the sponsored program.

፫/ በስፖንሰሩና በብሮድካስተሩ መካከል ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር ስፖንሰር በተደረገ ፕሮግራም ጣልቃ ሌላ የንግድ ማስታወቂያ መሰራጨት የለበትም፡፡ ስፖንሰር አድራጊዎች ከአንድ በላይ ሲሆኑ ሁሉም መፍቀድ አለባቸው።

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳፭ እና አንቀፅ ፳፮ መሰረት ማስታወቂያ እንዳይነገርለት የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ምርትን የሚያመርት ወይም የሚሸጥ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ማስታወቂያው እንዳይሰራጭ ለተከለከለበት የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ ስፖንሰር ሊሆን አይችልም፡፡

፭/ የፖለቲካ ድርጅቶች እና የሃይማኖት ተቋማት ስፖንሰር ሊሆኑ አይችሉም፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው በማናቸውም የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ ስፖንሰር ተደርጎ በሚሰራጭ ማስታወቂያ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ፲፮. ስፖንሰር የማይደረግ ፕሮግራም

፩/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውይይቶችን የሚያሠራጩ ፕሮግራሞች፣ የዜና ፕሮግራሞች እና የወቅታዊ ጉዳይ ዘገባ ፕሮግራሞች ስፖንሰር መደረግ የለባቸውም።

፪/ የሕጻናት ፕሮግራም በንግድ ድርጅት አማካኝነት ስፖንሰር መደረግ የለበትም።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የስፖርት ዜና፣ የአየር ሁኔታ ትንበያ እና የቢዝነስ ዘገባዎች ከሌሎች ዜናዎች ተለይተው የሚቀርቡ ከሆነ ስፖንሰር ሊደረጉ ይችላሉ።

# ክፍል አምስት

# በተለያዩ የማሰራጫ መንገዶች ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ

## ፲፯. በብሮድካስት አገልግሎት ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ

፩/ ማስታወቂያ ለማሰራጨት የተቋቋመ የብሮድካስት አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር በብሮድካስት አገልግሎት ተጓዳኝ፣ በፕሮግራም መልክ የሚሠራጭ ማስታወቂያን፣ የስፖንሰር አድራጊውን ስም፣ አላማ፣ አገልግሎት፣ ምርት እና መሰል መልእክቶችን እንዲሁም የምስጋና መግለጫን ጨምሮ ለማናቸውም ማስታወቂያ የሚመደበው ጊዜ፡-

ሀ) ከእለቱ ፕሮግራም ወይም ከአንድ የተለየ ፕሮግራም የስርጭት ጊዜ ውስጥ ከ፳ በመቶ፤

3/ Unless otherwise an agreement is concluded between the sponsor and the broadcaster, other commercial advertisement may not be disseminated in a sponsored program. When there are more than one sponsor, all of them shall give their consent.

4/ A person who produces or sells a product or renders a service whose advertisement is prohibited or restricted under Article 25 and Article 26 of this Proclamation may not sponsor a means of advertisement dissemination subject to the prohibition.

5/ Political and religious organizations may not be sponsors.

6/ The provisions of this Article shall be applicable, as deemed appropriate, to sponsored advertisements disseminated through any means of advertisement dissemination.

## 16. Programs not to be Sponsored

1/ Programs disseminating discussions of the House of Peoples' Representatives, news programs and current affairs programs may not be sponsored.

2/ Children's program may not be sponsored by a business organization.

3/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, sport, meteorology and business news may be sponsored if they are presented separately from other news.

# PART FIVE

# ADVERTISEMENT DISSEMINATION THROUGH DIFFERENT MEANS OF DISSEMINATION

## 17. Advertisement Dissemination through Broadcasting Service

1/ Unless it is broadcasting service station established for disseminating advertisement, the time to be allocated by a broadcasting service for any advertisement including split-screen, and infomercial advertisement, the name, objective, service, goods and similar messages as well as acknowledgement of a sponsor may not exceed:

a) 20% of its daily or a particular program transmission time;

ለ) ከአንድ ሰዓት በታች የቆይታ ጊዜ ካለው ከአንድ የተለየ ፕሮግራም የስርጭት ጊዜ ውስጥ ከ፲፭ በመቶ፤ ወይም

ሐ) በአንድ ሰዓት የስርጭት ጊዜ ከ፲፪ ደቂቃ፤

መብለጥ የለበትም፡፡

፪/ ማንኛውም ተጓዳኝ ማስታወቂያ፡-

ሀ) በምስል ወይም በፎቶግራፍ የሚሰራጭ ሲሆን የማስታወቂያው የስፍራ ሽፋን የቴሌቪዥኑ መስኮት ወይም የስክሪኑ ፍሬም ከሚሸፍነው ጠቅላላ ስፍራ ከ፲፭ በመቶ፤ ወይም

ለ) ተንቀሳቃሽ ተነባቢ መስመር ሆኖ የሚሰራጭ ሲሆን የማስታወቂያው ስፍራ ሽፋን የቴሌቪዥኑ መስኮት ወይም የስክሪኑ ፍሬም ከሚሸፍነው ጠቅላላ ስፍራ ከ፯ በመቶ፤

መብለጥ የለበትም፡፡

፫/ የሚከተሉት ፕሮግራሞች በማስታወቂያ መቋረጥ የለባቸውም፡-

ሀ) የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውይይት፤

ለ) የሕፃናት ፕሮግራም፤

ሐ) የዜና ወይም የወቅታዊ ጉዳይ ዘገባ፤

መ) የቅጅ መብት ባለቤቱ ካልፈቀደ በስተቀር ሙዚቃ፣ ድራማ ወይም ዶክሜንተሪ ፊልም፤

ሠ) የስርጭት ጊዜው ከ፳ ደቂቃ የማይበልጥ ማንኛውም ፕሮግራም፡፡

፬/ በአንድ ሰዓት የስርጭት ጊዜ ውስጥ የአንድን ምርት ወይም አገልግሎት ተመሳሳይ የንግድ ማስታወቂያ ከሁለት ጊዜ በላይ ማሰራጨት አይቻልም፡፡

፭/ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውይይት፣ በሕጻናት፣ በዜና ወይም በወቅታዊ ጉዳይ ዘገባ ፕሮግራም ውስጥ ተካታች ማስታወቂያ እንዲኖር ማድረግ አይቻልም፡፡

## ፲፰. በፕሮግራም መልክ የሚሰራጭ ማስታወቂያ

፩/ ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት በፕሮግራም መልክ የሚሠራጭ ማስታወቂያን ማሰራጨት ይችላል፡፡

b) 15% of a particular program having a transmission time of not more than one hour; or

c) 12 minutes in a one-hour transmission time.

2/ Where a split-screen advertisement is disseminated:

a) in the form of image or photograph, the space occupied by the advertisement may not exceed 15% of the total space covered by the television window or the screen frame; or

b) in the form of readable moving line, the space occupied by the advertisement may not exceed 7% of the total space covered by the television window or the screen frame.

3/ The following programs may not be interrupted by advertisement:

a) discussion of the House of Peoples' Representatives;

b) children's program;

c) news or current affairs program;

d) unless authorized by the copy right owner, music, drama or documentary film;

e) any program the transmission time of which is not more than 20 minutes.

4/ The same advertisement of a product or service may not be disseminated more than twice in a one-hour transmission time.

5/ An inserted advertisement may not be included in any discussion of the House of Peoples' Representatives, children's program, news or current affairs program.

## 18. Infomercials

1/ Any broadcasting service may disseminate infomercial.

፪/ ማስታወቂያ ለማሰራጨት የተቋቋመ የብሮድካስት አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር በፕሮግራም መልክ የሚሠራጭ ማስታወቂያ ከሌሎች ፕሮግራሞች የተለየ መሆኑ በግልፅ እንዲታወቅ ለማድረግ የሚያስችል ርዕስ ይዞ መቅረብ አለበት፡፡

## ፲፱ በማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ስለሚሠራጭ ማስታወቂያ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯(፩) የተደነገገው ቢኖርም በማንኛውም የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ተጓዳኝ፣ በፕሮግራም መልክ የሚሰራጭ ማስታወቂያን፣ የስፖንሰር አድራጊውን ስም፣ አላማ፣ አገልግሎት፣ ምርት እና መሰል መልእክቶችን እንዲሁም የምስጋና መግለጫን ጨምሮ ለማንኛውም ማስታወቂያ የሚመደበው ጊዜ፡-

፩/ ከእለቱ ፕሮግራም ወይም ከአንድ የተለየ ፕሮግራም የስርጭት ጊዜ ውስጥ ከ፲፭ በመቶ፣ ወይም

፪/ በአንድ ሰዓት የስርጭት ጊዜ ከ፱ ደቂቃ፣

መብለጥ የለበትም፡፡

## ፳. በጋዜጣና መጽሔት ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ

ማስታወቂያ ለማሰራጨት ብቻ የተቋቋመ ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም ጋዜጣ ወይም መጽሔት ላይ የሚሰራጩ ማስታወቂያዎች፡-

፩/ ከእያንዳንዱ እትም ጠቅላላ የሕትመት ሽፋን ከ፷ በመቶ የሚበልጠውን መያዝ የለባቸውም፣

፪/ ከሌሎች የሕትመቱ ውጤቶች የተለዩ መሆናቸው በግልፅ እንዲታወቅ “ማስታወቂያ” በሚል ርዕስ ሥር መቅረብ አለባቸው፡፡

## ፳፩. ስለውጭ ማስታወቂያ

፩/ ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው የመንግስት አካል ፈቃድ ሳያገኝና እንደ አግባብነቱ ባለቤቱ ወይም ባለይዞታው ሳይስማማ፡-

ሀ) በማንኛውም ሕንጻ፣ ግድግዳ፣ አጥር፣ የአውቶብስ ፌርማታ፣ ምሰሶ፣ የቴሌኮም አገልግሎት መስጫ መሣሪያ ወይም ሌሎች መሰል ነገሮች ላይ፣

2/ Unless it is a broadcasting service established for disseminating advertisement, an infomercial shall have a title that clearly differentiates it from other programs.

## 19. Advertisement Dissemination through Community Broadcasting Service

Notwithstanding to the provisions of Article 17(1) of this Proclamation, the time to be allocated by a community broadcasting service for any advertisement including split-screen, and infomercial the name, objective, service, goods and similar messages as well as acknowledgement of a sponsor may not exceed:

1/ 15% of its daily or a particular program transmission time; or

2/ 9 minutes in a one-hour transmission time.

## 20. Advertisement Dissemination through Newspapers and Magazines

Unless it is a newspaper or magazine established only to disseminate advertisement, advertisements disseminated through newspapers and magazines:

1/ may not exceed 60% of the whole content of each edition;

2/ shall appear under the title “advertisement” to distinguish them from the other materials of the periodical.

## 21. Outdoor Advertisement

1/ No person, unless obtained a permit from the appropriate government body and, as may be appropriate, the consent of the owner or possessor thereof, may affix, hang, erect or otherwise place outdoor advertisement on:

a) any building, wall, fence, bus station, pole, telecom service equipment or any other similar structure;

ለ) በማንኛውም መንገድ፣ አውራጎዳና፣ የባቡር ሀዲድ ወይም የሕዝብ መጓጓዣ ላይ፤ ወይም

ሐ) በማንኛውም የሕዝብ አገልግሎት በሚሰጥ ሥፍራ ላይ፤

የውጭ ማስታወቂያ መለጠፍ፣ መስቀል፣ መትከል ወይም በሌላ መንገድ ማስቀመጥ አይችልም፡፡

፪/ ማንኛውም የውጭ ማስታወቂያ ከመንገድ ምልክት ወይም አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክት ጋር በሚመሳሰል፣ እይታን በሚጋርድ፣ የትራፊክ እንቅስቃሴን በሚገታ ወይም ደህንነቱን በሚቀንስ ወይም የአካባቢን ገጽታና ውበት በሚያበላሽ መልኩ መቀመጥ የለበትም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀመጥ የውጭ ማስታወቂያ በአገር ውስጥ ቋንቋ ወይም ፊደል የተጻፈ መሆን ወይም በውጭ ቋንቋ ወይም ፊደል ጭምር የተጻፈ ሲሆን የአገር ውስጥ ቋንቋው ወይም ፊደሉ ከውጭው ቋንቋ ወይም ፊደል አስቀድሞ ወይም ከላይ ሆኖ የተጻፈ መሆን አለበት፡፡

## ፳፪. በስልክ አገልግሎት ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ

፩/ በስልክ አገልግሎት አማካኝነት ማስታወቂያ ለማሰራጨት የሚቻለው የቴሌኮም አገልግሎትን ከሚሰጠው አካል የተሰጠ ፈቃድ ሲኖር ነው፡፡

፪/ የሕዝብ ማስታወቂያ ወይም የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪውን የሚመለከት ማስታወቂያ ካልሆነ በስተቀር የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚው ሳይፈቅድ ማንኛውም የንግድ ማስታወቂያ በስልክ አገልግሎት ተጠቃሚው የስልክ አገልግሎት መስጫ መሳሪያ ማሰራጨት የተከለከለ ነው።

፫/ የማስታወቂያ ወኪሉ፣ የማስታወቂያ አሰራጩ እና አስነጋሪው ለስልክ አገልግሎት ተጠቃሚው የሚያሰራጨት ማስታወቂያ ክፍያ የሚከፈልበት ከሆነ ለተጠቃሚው በግልፅ ማሳወቅ አለባቸው።

## ፳፫. በፖስታ አገልግሎት ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ

፩/ በፖስታ አገልግሎት አማካኝነት ማስታወቂያ ለማሰራጨት የሚቻለው የፖስታ አገልግሎትን ከሚሰጠው አካል የተሰጠ ፈቃድ ሲኖር ነው፡፡

b) any road, highway, rail way or public transport; or

c) any place used for public services.

2/ Any outdoor advertisement may not be placed in such a way as to be confused with traffic or direction signs, obstruct views, hamper or undermine traffic movement or safety, or spoil beauty of the scenery.

3/ Any outdoor advertisement placed in accordance with this Article shall be written in local language or alphabet, or if it is written in local and foreign languages or alphabets, the local language or alphabet shall appear before or above the foreign language or alphabet.

## 22. Advertisement Dissemination through Telephone

1/ Any advertisement through telephone shall be disseminated with the permission of the telecom service provider.

2/ With the exception of public advertisements and advertisements of the telecom service provider, disseminating any commercial advertisement through the apparatus of a telephone service user, without his consent, shall be prohibited.

3/ If the dissemination of the advertisement requires the telephone service user to pay charges, the advertising agent, advertisement disseminator and advertiser shall make it clear to the telephone service user.

## 23. Advertisement Dissemination through Postal Services

1/ An advertisement through postal service shall be disseminated by obtaining permission from the postal service provider.

፪/ የፖስታ አገልግሎት ሰጪው የሕዝብ ማስታወቂያን ወይም የፖስታ አገልግሎት ሰጪውን የሚመለከት ማስታወቂያን በፖስታ አገልግሎት ተጠቃሚ የፖስታ ሳጥን ማሰራጨት ይችላል፤ ሆኖም በፖስታ አገልግሎት ተጠቃሚ የፖስታ ሳጥን የንግድ ማስታወቂያን ለማሰራጨት የፖስታ አገልግሎት ተጠቃሚውን ፍላጐት ከግምት ውስጥ ማስገባትና አሰራር መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

## ፳፬. በሲኒማ ወይም በፊልም ስለሚሰራጭ ማስታወቂያ

የሲኒማ ወይም የፊልም ትእይንትን በየእረፍት ሰዓቱ ወይም በየትእይንቱ ምዕራፍ ጣልቃ ካልሆነ በስተቀር በማስታወቂያ ማቋረጥ ክልክል ነው፡፡

## ክፍል ስድስት

## የተከለከሉና ገደብ የተደረገባቸው ማስታወቂያዎች

## ፳፭. የተከለከለ ማስታወቂያ

፩/ የሚከተሉትን ማስታወቂያዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በማንኛውም የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡-

ሀ) አግባብ ባለው የመንግስት አካል በአደንዛዥ እፅነት የተመደበን ማንኛውንም እፅ የሚመለከት ማስታወቂያ፤

ለ) ያለሐኪም ትእዛዝ የማይሰጥ ወይም በጥቅም ላይ የማይውል መድሀኒትን ወይም የሕክምና መገልገያን ተጠቃሚው በቀጥታ እንዲጠቀም የሚገፋፋ ማስታወቂያ፤

ሐ) ናርኮቲክ መድሐኒትን ወይም ሳይኮቱራፒክ ንጥረ ነገርን የሚመለከት ማስታወቂያ፤

መ) የጦር መሳሪያ ማስታወቂያ፤

ሠ) የቁማር ማስታወቂያ፤

ረ) የሕገ ወጥ ምርት ወይም አገልግሎት ማስታወቂያ፤

ሰ) የአራጣ አበዳሪ ማስታወቂያ፤

ሸ) የጥንቆላ ማስታወቂያ፤

ቀ) የሲጋራ ወይም የሌሎች የትምባሆ ውጤቶች ማስታወቂያ፤

በ) የፖለቲካ ግብ ያለው ማስታወቂያ፤ እና

ተ) ሌሎች በሕግ የተከለከሉ ማስታወቂያዎች፡፡

2/ A postal service provider may disseminate public advertisement or its own advertisement through the post box of a postal service user; provided, however that, to dessiminate a commercial advertisement through the post box of a postal service user, a postal service provider shall take in to consideration the interest of a postal service user and establish a working procedure.

## 24. Advertisement Dissemination through Cinema or Film

Unless during break time or end of a scene, interruption of any cinema or film for advertisement shall be prohibited.

## PART SIX

## PROHIBITED AND RESTRICTED ADVERTISEMENTS

## 25. Prohibited Advertisement

1/ The direct or indirect dissemination of the following advertisements through the use of any means of dissemination shall be prohibited:

a) advertisement of any substance classified as narcotic drug by appropriate governmental body;

b) advertisement that encourage the direct use of any prescription medicine or medical appliance;

c) advertisement of narcotic drug or psychotropic substance;

d) advertisement of weapon;

e) advertisement of gambling;

f) advertisement of illegal product or service;

g) advertisement of usury;

h) advertisement of witchcraft;

i) advertisement of cigarette or other tobacco products;

j) advertisement having political goals; and

k) other advertisements prohibited by law.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(በ) የተደነገገው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የምርጫ እጩ ተወዳዳሪ በምርጫ ወቅት የሚያሰራጨውን የምርጫ ውድድር ማስታወቂያ እንዲሁም የፖለቲካ ድርጅቱ የሚያሰራጨውን የአድራሻ ለውጥ፣ የስብሰባ ጥሪ እና መሰል ማስታወቂያዎችን የሚከለክል አይደለም።

**፳፮. <u>ገደብ የተደረገበት ማስታወቂያ</u>**

፩/ የአልኮል መጠኑ ከ፲፪ በመቶ በላይ የሆነ ማንኛውንም መጠጥ የሚመለከት ማስታወቂያ ከውጭ ማስታወቂያ እና እለታዊና ሳምንታዊ ካልሆነ ጋዜጣ እና መጽሔት በስተቀር በሌሎች የማስታወቂያ ማሰራጫ መንገዶች አማካኝነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማሰራጨት የተከለከለ ነው፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የአልኮል መጠኑ ከ፲፪ በመቶ በላይ የሆነ የማንኛውም መጠጥ ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክ ስክሪን፣ በድምፅ ማጉያ፣ በድምፅ ካሴት ወይም በሌላ በምስልና በድምፅ በሚሰራጭ የውጭ ማስታወቂያ ሊሰራጭ አይችልም፡፡

፫/ ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ማስታወቂያ፡-

ሀ) የአልኮል መጠጡን መውሰድ ለጤና ተስማሚ እንደሆነ፣ ግላዊ ወይም ማኅበራዊ ስኬትን እንደሚያስከትል፣ የተሻለ ሥነ ልቦናዊ ወይም አካላዊ ብቃት እንደሚያስገኝ ወይም ፈዋሽ እንደሆነ የሚገልጽ ወይም በተደጋጋሚ ወይም ከልክ በላይ እንዲጠጣ የሚገፋፋ፤

ለ) ከአልኮል ሱስ መጠበቅን የሚያጣጥል ወይም የሚቃወም፤

ሐ) አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ወይም አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን የማስታወቂያው ተዋናይ አድርጎ የሚጠቀም፤ ወይም

መ) ሌላ መሰል መልእክት የሚያስተላልፍ፤

መሆን የለበትም፡፡

፬/ የማንኛውም የአልኮል መጠጥ የውጭ ማስታወቂያ ከልጆች መዋያ ማዕከል፣ ከትምህርት ቤት፣ ከህክምና ወይም ታሪካዊ ተቋም፣ ከሲኒማ ቤት፣ ከቲያትር ቤት ወይም ከስታዲየም በመቶ ሜትር ራዲየስ ውስጥ እንዲቀመጥ መደረግ የለበትም፡፡



2/ The provisions of sub-article (1)(j) of this Article may not preclude a political organization or a candidate registered in accordance with the law from advertising the election campaign, or the political organization from advertising change of its address, meeting announcement and from disseminating other similar advertisements.

**26. <u>Restricted Advertisement</u>**

1/ Any advertisement of liquor with more than 12% alcoholic content may not be disseminated directly or indirectly through any means of dissemination other than outdoor advertisements and news papers and magazines which are not published on daily and weekly basis.

2/ Notwithstanding to the provision of sub-article (1) of this Article, the advertisement of any liquor with more than 12% alcoholic content may not be disseminated through the use of electronic screen, microphone, audio cassette, or other audiovisual advertisement disseminated through the use of outdoor advertisement.

3/ Any advertisement of liquor may not:

a) advertise that consumption of the liquor is good for health, brings about individual or social success, improves psychological or physical strength or provides healing power, or instigate its repeated consumption or over drinking;

b) undermine or oppose abstention from alcohol addiction;

c) concentrate on minors, or use a minor as an advertisement actor; or

d) contain other similar massages.

4/ An outdoor advertisement of any liquor may not be placed within 100 meters radius of a children care center, school, medical or historical institution, cinema or theater hall or a stadium.

## ክፍል ሰባት

### የማስታወቂያ አስነጋሪ፣ የማስታወቂያ ወኪል እና የማስታወቂያ አሰራጭ ግዴታዎች

### ፳፯. መረጃን ስለማረጋገጥ

፩/ ማንኛውም የማስታወቂያ ወኪል ወይም አሰራጭ፡-

ሀ) በማስታወቂያ እንዲሰራጭ በማስታወቂያ አስነጋሪ የቀረበለትን መረጃ ትክክለኛነት የማረጋገጥ፣ እና

ለ) ማስታወቂያው በቀረበው መልኩ ቢሠራጭ ሕግን የሚተላለፍ ውጤት የሚያስከትል ከሆነ ይህንኑ እንዲያስተካክል ለማስታወቂያ አስነጋሪው የማሳወቅ፣

ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የማስታወቂያ አስነጋሪ በማስታወቂያው ውስጥ ያካተተውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በማስታወቂያ ወኪሉ ወይም አሰራጩ እንዲያቀርብ የሚጠየቀውን ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

፫/ ማስታወቂያ አስነጋሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ) ወይም (፪) መሠረት የተጠየቀውን ለማሟላት ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም ካልቻለ የማስታወቂያ ወኪሉ ወይም አሰራጩ ከማስታወቂያ አስነጋሪው ጋር የገባውን ውል በመሰረዝ ለደረሰበት ኪሳራ ካሳ እንዲከፈለው መጠየቅ ይችላል፡፡

### ፳፰. ሪኮርድ ስለመያዝና መረጃ ስለመስጠት

፩/ ማንኛውም የማስታወቂያ አስነጋሪ፣ የማስታወቂያ ወኪል ወይም የማስታወቂያ አሰራጭ የእንድን የተሰራጨ ማስታወቂያ ቅጅ ሪኮርድ ቢያንስ ለስድስት ወራት ይዞ ማቆየት አለበት፡፡

፪/ ማንኛውም የማስታወቂያ አስነጋሪ፣ የማስታወቂያ ወኪል ወይም የማስታወቂያ አሰራጭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተያዘውን የማስታወቂያ ሪኮርድ ቅጅ በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የመንግሥት አካል ከዚህ አዋጅ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ምክንያት እንዲያቀርብ ሲጠየቅ በራሱ ወጪ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡



## PART SEVEN

### OBLIGATIONS OF ADVERTISER, ADVERTISING AGENT AND ADVERTISEMENT DISSEMINATOR

### 27. Verification of Information

1/ Any advertising agent or advertisement disseminator shall have the obligation:

a) to verify the correctness of an information provided to it by an advertiser; and

b) to require the advertiser to make adjustments to an advertisement where it breaches the law if disseminated as presented.

2/ Any advertiser shall have the obligation to submit evidence requested by an advertising agent or disseminator to verify the correctness of an information included in an advertisement.

3/ The advertising agent or disseminator may cancel the contract concluded with the advertiser and claim damages if the advertiser is unwilling or unable to fulfill the requirement specified under sub-article (1)(b) or (2) of this Article.

### 28. Record Keeping and Providing Information

1/ Any advertiser, advertising agent or advertisement disseminator shall have the obligation to make a copy of a disseminated advertisement and keep a record of it at least for six months.

2/ Any advertiser, advertising agent or advertisement disseminator shall, when requested by the Authority or the appropriate government body in connection with the enforcement of this Proclamation, provide, at its own cost, a copy of an advertisement record kept in accordance with sub-article (1) of this Article.

**፳፱. ማስታወቂያን በፍትሃዊነት ስለማሰራጨት**

ማንኛውም ማስታወቂያ የሚያሰራጭ የመገናኛ ብዙሃን ከማስታወቂያ አስነጋሪዎች እና ከማስታወቂያ ወኪሎች የሚቀርቡለትን ማስታወቂያዎች ያለአድልዎና በፍትሃዊነት ማሰራጨት አለበት።

**፴. የማስታወቂያ አስነጋሪ፣ የማስታወቂያ ወኪል እና የማስታወቂያ አሰራጭ ሃላፊነት**

ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር የዚህ አዋጅ ድንጋጌን በመተላለፍ የተሰራጨ ማስታወቂያ በማስታወቂያ አስነጋሪው፣ በማስታወቂያ ወኪሉ እና በማስታወቂያ አሰራጩ ፈቃድ እንደተሰራጨ ተቆጥሮ እንደሃላፊነታቸው መጠን በአንድነት ወይም በነጠላ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፴፩. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ማስታወቂያ ለአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እድገት አስተዋፆ ሊያበረክት በሚችል መልኩ መካሄዱን ያረጋግጣል፤

፪/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር የማስታወቂያ ሥራ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት እና የሥነ ምግባር መመሪያ ያወጣል፤

፫/ የውጭ ማስታወቂያን ሳይጨምር የዚህን አዋጅ ድንጋጌ በመተላለፍ የተሰራጨን ማንኛውንም ማስታወቂያ ይመረምራል፣ ያግዳል፤ የአፀፋ ማስታወቂያ እንዲወጣ ያዛል፤

፬/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በተሰራጨ ማስታወቂያ ጥፋት በፈጸመ ሰው ላይ የወንጀል ክስ ለመመስረት የሚረዳን መረጃ አግባብ ላለው የመንግስት አካል ያስተላልፋል፤

፭/ የውጭ ማስታወቂያዎችን በሚመለከት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መከበራቸውን በማረጋገጥ ረገድ ለሚመለከታቸው የክልል አካላት የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

፮/ የማስታወቂያ ሙያ የሚያድግበትን ስልትና ዘርፉ ራሱን በራሱ የሚቆጣጠርበትን ሁኔታ ይቀይሳል፤ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።

**29. Fair Dissemination of Advertisements**

Any mass media disseminating advertisements shall disseminate impartially and fairly advertisements submitted to it by advertisers and advertising agents.

**30. Responsibilities of Advertiser, Advertising Agent and Advertisement Disseminator**

Unless proved to the contrary, any advertisement disseminated in breach of the provisions of this Proclamation shall be presumed to have been conducted with the consent of the advertiser, advertising agent and advertisement disseminator, and they shall be jointly and severally liable according to their degree of responsibility.

## PART EIGHT

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**31. Powers and Duties of the Authority**

The Authority shall have the powers and duties to:

1/ ensure that advertisement is conducted in such a manner that contributes to the economic, social and political development of the country;

2/ in consultation with the appropriate bodies, issue competency requirement and code of conduct for advertising activity;

3/ examine and suspend any advertisement, other than outdoor advertisement, disseminated in violation of the provisions of this Proclamation, and order the dissemination of a counter advertisement;

4/ transmit to the appropriate government body any information relevant for the prosecution of any offender who disseminated an advertisement in violation of the provisions of this Proclamation;

5/ provide technical support to the appropriate regional bodies regarding the enforcement of this Proclamation with respect to outdoor advertisements;

6/ design strategies and provide support for developing the advertising profession and for making the sector self regulated.

**፴፪. <u>የሸማቾች ማኅበር</u>**

አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም የሸማቾች ማኅበር፦

፩/ ይህን አዋጅ በማስፈጸም ረገድ ከባለሥልጣኑና ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር ይተባበራል፤

፪/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌ በመተላለፍ በተሰራጨ ማስታወቂያ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውን አባላቱን በመወከል የፍትሐ ብሔር ክስ የመመስረት መብት ይኖረዋል፡፡

**፴፫. <u>ለባለሥልጣኑ ስለሚቀርብ አቤቱታ</u>**

፩/ ከውጭ ማስታወቂያ በስተቀር የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በተሰራጨ ማንኛውም ማስታወቂያ መብቱ የተጣሰ ሰው የማስታወቂያው ስርጭት እንዲታገድለት ወይም የአፀፋ ማስታወቂያ እንዲወጣለት ማስታወቂያው ከተሰራጨበት ቀን ጀምሮ ባለው የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ሥልጣን ላለው የዳኝነት አካል ክስ ማቅረብን የሚከለክል አይሆንም፡፡

**፴፬. <u>ቅጣት</u>**

፩/ በሌላ ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፦

ሀ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፭(፩) እና (፪) በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፮/፪ሺ፪ አንቀጽ ፷(፩) መሠረት ይቀጣል፤

ለ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፭(፫)፣ አንቀጽ ፭(፭)፣ አንቀጽ ፮(፪)፣ አንቀጽ ፮(፫)፣ አንቀጽ ፮(፬)፣ አንቀጽ ፲፣ አንቀጽ ፲፩፣ አንቀጽ ፲፪(፪)፣ አንቀጽ ፲፫፣ አንቀጽ ፲፭(፩)፣ አንቀጽ ፲፭(፪)፣ አንቀጽ ፲፭(፫)፣ አንቀጽ ፲፮፣ አንቀጽ ፲፯፣ አንቀጽ ፲፰፣ አንቀጽ ፲፱፣ አንቀጽ ፳፣ አንቀጽ ፳፩፣ አንቀጽ ፳፪፣ አንቀጽ ፳፫፣ አንቀጽ ፳፬፣ አንቀጽ ፳፮(፫)፣ አንቀጽ ፳፯፣ አንቀጽ ፳፰ ወይም አንቀጽ ፳፱ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር ፲ሺ በማያንስና ከብር ፩፻ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

**32. <u>Consumers Association</u>**

Any consumers association established under the relevant law shall:

1/ cooperate with the Authority and the appropriate government bodies in the enforcement of this Proclamation;

2/ have the right to institute a civil suit on behalf of its members who have sustained damages as a result of an advertisement disseminated in violation of the provisions of this Proclamation.

**33. <u>Submission of Complaints to the Authority</u>**

1/ Any person whose rights are infringed by the dissemination of any advertisement, other than outdoor advertisement, in violation of the provisions of this Proclamation may submit complaints, within six months from the date of the dissemination of the advertisement, to the Authority to obtain an order of suspension of disseminating the advertisement or the dissemination of a counter advertisement.

2/ The provision of sub-article (1) of this Article may not be construed to preclude the institution of a suit with the competent judicial body.

**34. <u>Penalty</u>**

1/ Unless punishable with more severe penalty under other law, any person found guilty of violating:

a) Article 5(1) and (2) of this Proclamation shall be punishable in accordance with Article 60(1) of the Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 686/2010;

b) Article 5(3), Article 5(5), Article 6(2), Article 6(3), Article 6(4), Article 10, Article 11, Article 12(2), Article 13, Article 15(1), Article 15(2), Article 15(3), Article 16, Article 17, Article 18, Article 19, Article 20, Article 21, Article 22, Article 23, Article 24, Article 26(3), Article 27, Article 28 or Article 29 of this Proclamation shall be punishable with a fine not less than Birr 10,000 and not exceeding Birr 100,000;

ሐ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፮(፩)፣ አንቀጽ ፯፣ አንቀጽ ፰፣ አንቀጽ ፱፣ አንቀጽ ፲፪(፩)፣ አንቀጽ ፲፬፣ አንቀጽ ፲፭(፬)፣ አንቀጽ ፲፭(፭)፣ አንቀጽ ፳፮(፩)፣ አንቀጽ ፳፮(፪) ወይም አንቀጽ ፳፮(፬) በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር ፳ሺ በማያንስና ከብር ፩፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

መ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፳፭(፩) በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው ከብር ፴ሺ በማያንስና ከብር ፪፻፶ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው የገንዘብ መቀጮ በተጨማሪ ጥፋተኛ የሆነው ሰው ከሕገ ወጥ ማስታወቂያ ሥራው ያገኘው ገቢ ይወረሳል፡፡

## ፴፭. ተፈፃሚነት ስለማይኖረው ሕግ

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## ፴፮. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፫/ ክልሎች የውጭ ማስታወቂያን በሚመለከት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችንና መመሪያዎችን ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

## ፴፯. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፯ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

c) Article 6(1), Article 7, Article 8, Article 9, Article 12(1), Article 14, Article 15(4) , Article 15(5), Article 26(1), Article 26(2) or Article 26(4) of this Proclamation shall be punishable with a fine not less than Birr 20,000 and not exceeding Birr 150,000;

d) Article 25(1) of this Proclamation shall be punishable with a fine not less than Birr 30,000 and not exceeding Birr 250,000.

2/ In addition to the fine specified under sub-article (1) of this Article, the income obtained by the convicted person from the illegal advertisement activity shall be confiscated.

## 35. Inapplicable Law

No law or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with the provisions of this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

## 36. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Authority may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued under sub-article (1) of this Article.

3/ Regions may issue regulations and directives necessary for the implementation of this Proclamation with respect to outdoor advertisements.

## 37. Effective date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of August, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**